# ውሸትን ፍለጋ

## አንድ

Dejat Kassa

ይህ ታሪካዊ ፅሁፍ ልጅ ኢያሱ ሚካኤልን ከስልጣን ለመገፍተር የተቀነባበረ ነው። መፈንቅለ መንግስትን ለማሳካት የተዘጋጀ። በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የተመለከቱት ውሸቶች፣ የስም ማጥፋት ዘመቻዎችና በህዝብ ስም ማጭበርበሮች የኢህኣዴግን መንግስት ለመገፍተር ከሚነዙት ውሸቶች፣ የስም ማጥፋት ዘመቻዎችና በህዝብ ስም የማጭበርበር ሙከራዎች ጋር ያላቸው ተመሳሳይነት "ውሸትም ይወረሳል እንዴ?" ያስብላል።

". . . ከሱ ፈቃድ የወጣ ሰው ርጉም ይሁን፣ ጥቁር ውሻ ይውለድ፤..." የሚለውን ቃል ". . . እሱን የዋሸ ዋሾ ይሁን፤ ውሸታምም ይውለድ፤..." ቢሆን ኖሮ ቃሉ መድረሱ ለማንም ግልፅ ይሆን ነበር። ያም ሆነ ይህ መኳንንቶቹ ልጅ እያሱን በመበደላቸው ጥቋቁር ውሾች ባይወልዱም፥ መዋሸታቸው ብድር በምድር ሆነና ኢትዮጵያ ኣገራቸው ብዙ ውሸታሞች ተወልደውባታል። ለውሸትም በውሸትም የሚኖሩ፤ ለውሸትም በውሸትም የሚሞቱ።

ባሽከሮቼ ክፋት ደግሞ ባጋፋሪ፤
ዘውዱ ቲዞር ኣየን ወደ ልጅ ተፈሪ።
ሸኽ ሁሴን ጅብሪል

### ፲፱፻፱ ዓመት ምህረት፥ መስከረም ፲፯ ቀን።

ልጅ እያሱ የጃንሆይ ያጼ ምኒልክ ትእዛዝ ስላፈረሱ፥ ያባታችንን ያቡነ ማቴዎስን፥ የእጨጌ ወልደ ጊዮርጊስንም የመሓላንና የግዝትን ቃል ስለጣሱ፥ መኳንንቱም፥ ሰራዊቱም፥ ህዝቡም ሁሉ ተሰብስቦ ላባታችን ላቡነ ማቴዎስና ለእጨጌ ወልደጊዮጊስ ያስታወቁበት የጩኸት ቃል ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈው ነው።

ጃንሆይ ኣጼ ምኒልክ፥ ለሃይማኖትዎና ለመንግስትዎ እጅግ ተጨናቂ ነበሩ። ቀድሞ እንዳለፉት ነገስታት ጊዜ ሰራዊታቸው እርስበርሱ እንዳይተላለቅባቸው፤ መንግስትዎም ንፋስ እንዳይገባበት ኣስበው፤ ፈፅመው እቤት ሳይውሉ፥ ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት፥ ሊቀጳጳሱና እጨጌ ቆማችሁ፤ መኳንንቱንና ህዝቡን ሰብስባችሁ፤ ልጄን እያሱን ሰጥቻቸዋለሁና ከሱ ፈቃድ የወጣ ሰው ርጉም ይሁን፣ ጥቁር ውሻ ይውለድ፤ እሱም እናንተን ያለኣግባብ የበደለ እንደሆነ ርጉም ይሁን፣ ጥቁር ውሻ ይውለድ ብለው ሰጡን። ኣባታችን እጨጌንም በዚሁ ቃል ኣውግዛችሁ ሰጠሁን። እኛም ደስ ብሎን ተቀብለን፥ የግዝትም ቃል እንዳይናወጥብን ተጠንቅቀን ባለንበት ኣገር ሁሉ፤ በትህትና ራሳችንን ደፍተን፥ በተቻለን በሙሉ ልባችን መንግስታችንን እየረዳን እስካሁን ቆየን። ከግዝትም ቃል የወጣ ስራ እንዳልሰራን፥ ኣባታችንም መላ ኢትዮጵያም ያውቃል።

## የምናመለክተውም ቃል ይኸው ነው።

### ፩ኛ

መገሥመሪያ ጃንሆይ ማረፋቸውን ሰው ሁሉ እያወቀው፥ ባረፉበት ሰሞን በልጅ እያሱ ትእዛዝ ሰው ሁሉ ፈረሱን እየጫነ ጉግስ ሲጫወት ሰነበተ። የቀረው ሁሉ ቢቀር፥ በዚያን ሰሞን ማዘንና መተከዝ ይገባ ነበር። መኳንንቱና ህዝቡም ለጌታው ሳያለቅስ እንባው እንዳረገዘ ቀረ። ምኒልክን የመሰለ የድሃ ኣባት፣ እናት የነጋሲው ንጉሳችን፥ መላ ኢትዮጵያን ኣንድ ኣድርገው፥ ኣስማምተው፥ ኣህዛብ ኣቅንተው ባጸኑት መንግስት፣ ባሰሩትም ኣብያተ ክርስቲያን፥ ጧፍ፣ ዕጣን ሳይባልላቸው ቀረ። ኣፅማቸውም የወደቀበትን ቦታ ኣባታችንም ያውቂታል። በጃንሆይ ማረፍ ህዝቡ በግልፅ እንዳይቀሰቀስ ማድረጋቸውና ኣለማስፈታታቸው፥ መንግስት እንዳይነቃንቅባቸው ይሆናል። ነተገ ዛሬ ፍታት ኣስፈቱ፣ ምፅዋትም ኣድርጉ ይሉናል እያልን ስንጠብቅ ይህን ያህል ቀን ቆየን። ያባታቸውንም ማረፍ ከምንም ሳይቆጥሩ የቀሩት ለካ ሃይማኖታቸውን ከለወጡ ብዙ ጊዚያቸው ኖሯል።

### ፪ኛ

ሃይማኖት መለወጣቸውንና ከክርስቲያን መንገድ መውጣታቸውን መግለፅ ከወጠኑት ዠምሮ፥ የሰሩትን ያልተገባ ስራ፥ ሁሉን ፅፈን ለመጨረስ ኣይቻልምና፥ ዋና ዋናውን ብቻ ባጭር ቃል እናመልክት።

ጌታችን ጃንሆይ የሮፓን ስርዓት እኔው ተሸቀዳድሜ ባገሬ ታላገባሁና፥ በሁሉም ነገር እነርሱን ካልመሰልኋቸው ኣይሆንም ብለው፥ ከተማ መጠበቁና የሮፓን ስርዓት ማለማመጃ ይሁን ብለው የሌሊት ዘበኛ ቢያቆሙም፤ ልጅ እያሱ ኣስር ኣስር ኣሽከር እያስከተሉ፥ ሌሊት እየዞሩ፥ እንደ ሽፍታ ከዘበኞቹ ጋር እየተታኰሱ፥ ጠንክረው የሚጠብቁትን ዘበኞች እየገደሉ፥ በከንቱ ደማቸውን እያፈሰሱ፥ የቆመውን ደንብ በገዛ እጃቸው ስላልረባ ነገር ኣፈረሱት።

### ፫ኛ

የእስላም ቃልቾች እየሰበሰቡ፥ የመሓመድንና የግራኝን ታሪክ ስያስነበቡ፤ ያያቶቻቸውን ዘር እየቆጠሩ፥ የይማሞች ዘር ከመሓመድ የወረደ ነው ኣሰኝተው፥ እስላምነታቸውን ካደላደሉ በኋላ የእስላም ሴት እየፈለጉ፥ ያባ ጅፋርን ልጅ፣ የእህቱን ልጅ፣ የዓሚር ዓብድላሂን ልጅ፣ የነጋድራስ መሓመድን ልጅ፣ ያዳልንም የባላባት ልጅ፤ እነዚህን ሁሉ ኣግብተው፥ ቁባቱ ሁሉ፥ የቀሩትማ የእስላም ሴቶች ስንቱ ተፅፈው ያልቃሉ። ስንኳስ ያልተጠመቀችዋንና ክርስቲያንዋንም ብትሆን በመፅሓፋችን የታዘዘ ኣለ።

### ፬ኛ

ኣባታችን እጨጌም፥ ይህ ሁሉ ስራ ሲሰራ እያወቁና እያሰቡ፥ መክረው ለመመለስ ተሸነፉ። ኣባታቸው ንጉስ ሚካኤል፥ ልጃቸውን መክረው ከዚህ ከክፉ መንገዳቸው ይመልሱልናል ብለን ተስፋ ስናደርግ ኣሸንፈዋቸው ኖሮ ኣምና በፍልሰታ የእስላም ጾም ገጥሞ ነበርና፥ ኣባታቸው ከተማ ደሴ ላይ የሰሩት የክህደት ስራ፥ በጅሌና በጥሙጋ፣ በጨኖ፣ በጅላሌ ሲያደርጉት የከረሙ ስራ ሁሉ ቢፅፉትም ኣያልቅ፤ ለመስማትም ደስ ኣያሰኝ። ይኸን ሁሉ ስራ ሲሰሩ መኳንንቱም ሰራዊቱም እያየ፥ እየሰማ፥ ሕፃን ቢሆን ነው እያለ ትእግስት ቢያበዛ፤ ልጅ እያሱ ዘውዳቸውን ጭነው፥ በክርስትና ፀንተው፥ መንግስታቸውን ጠብቀው

መያዝና ማጥናት ጠልተው፥ እድሜኣቸው ለእውቀት ሲደርስ፥ ሃያ ዓመት ሲሞላቸው፥ የቃልቻ ቃል እየሰሙ፥ በኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግስት አልቆአል፥ ከመሓመድና ከግራኝ ዘር የወረዱት የይማሞች መንግስት መነሻው ደርሷል እያሉ፥ ኣምና ሃረርጌ የወረዱ ጊዜ ኣራቱ ኣድባራት ቤተክርስቲያን ገብተው ኣንድ ግዜ እጅ ሳይነሱ ቀሩ። ከዚያ ሁሉ ኣብያተ ክርስቲያን ላንዱ እንኳ ገንዘብ ሳይሰጡ፥ የመላው ሃረርጌ እስላም እየተሰበሰበ የሚሰግድበት መስጊድ ሂደው ኣብረው ሰገዱ። ባምስቱም በር ዙርያ ላሉት መስጊዶችና ቃልቾች ኣትርሱን እያሉ ብዙ ገንዘብ ሰጡ።

፫ኛ

ጃንሆይ ሃረርጌን የሰበሩ ጊዜ ከክርስቲያን ሲዋጋ ያለቀው እስላም፥ ቦታውንና ቤቱን ሁሉ፥ ጃንሆይ በፍቃዳቸው ለመንግስት እርስት ይሁን ብለው፥ ለካህናትና ለከተማው ዘበኛ፥ ከከተማ ለማይለይ ሰራተኛ ሰጥተዉት፤ የፈረሰውን መልሶ እየሰራ፥ የዛባውን እያቀና፥ ይህንን ያህል ዘመን ይዞት የኖረውን ቤት፥ ለእስላሙ ልቀቁ ብለው ኣስለቀቁት። ካህናቱም ከታቦቱ ተለይቶ ወጣ። ድሃውም ኣልቅሶ ለቀቀ።

፬ኛ

ያሩሲ ጋላ ሸፍቶ፥ ፊታውራሪ ኣብተ ጊዮርጊስና ቢትወደድ ሃይለ ጊዮርጊስን ሽፍታውን ለማርጋት ጦር ቢልኩ፤ ይኸውም ከጥፋት ተቆጥሮባቸው ተነቀፉበት። ይኸም እስላም እንዳይነካ ለማድላት ነው። እንደዚሁም የመሰለ፥ በደጃዝማች ተፈሪ ግዛት በውጋዴን፥ ኣርባ ኣምስቱን ወታደር ሶማሌ ኣርዶት ስራት ሳይታይ፤ ይልቁንም ሶማሌዎቹ ኣዲስ ኣበባ ቢመጡ ተሸልመው ሄዱ። የክርስቲያንም ደም እንደውሻ ደም ሆኖ ቀረ። ይህም ነገር እስላም በክርስቲያን መቀባቱ ነው።

፭ኛ

ኣዲሱ ከተማ ድሬዳዋ ቀድሞ ያልነበረውን መስጊድ ተሰርቶ፥ ኣሁን ከዚህ ከወረዱ የእስላም ኣሊሞች ልብስ ለብሰው፥ የእስላም ጥምጣም ጠምጥመው፥ ግልድም ኣስገልድመው፥ ፈፅመው የክህደት ስራ ሰርተው፥ እመስጊድም ገብተው ኣብረው ሰገዱ። ለመስጊድም ብዙ ገንዘብ ሰጡ። የኛ ታቦት ግን ኣስቀድሞ ተቈርቍሮ በመቃኞ የኖረው፤ ካህናቱም መኳንንቱም ቢያስታውቁ፥ እስካሁን ሳይሰራ ቀርቶ፥ የመስጊድ ስራ በልጦ ቀደመው።

፮ኛ

ጅጅጋ ላይ ዳርቻ ኣገር ነው። በዚያ ውስጥ የሚቀመጥ ክርስቲያን መቅደስ ካልተተከለለት ሰውነቱ ይማግጣል ብለን የተከልነው ታቦት፥ ይህ ለመስጊድ የሚሆን ቦታ ነውና ታቦቱ ከሌላ ቦታ ሂዶ ይደረብ ብለው፥ ካህናቱም ታቦቱን ይዘው ጊሪ ከሚባል ቦታ ተዳብለው ተቀምጠዋል። ይህስ የእስላም ወገን ኣፅኚ ነኝ ማለት ኣይደለም? ኣሁን መጠቅለያውን የሃረርጌ መድሃኔኣለም ቤተክርስቲያን የተሰራበት፥ ቀድሞ መስጊድ ነበርና፥ ታቦቱ ይውጣና እንደ ጥንቱ መስጊድ ይሁን ብለው ነበር። በቅርብ ቀን ነገር የሚነሳባቸው ቢሆን፥ ለጊዜው ትተውታል። ለኋላው ግን የልባቸውን ሳይፈፅሙት ኣይቀሩም።

፱ኛ

ከዚህ ሁሉ የሚከፋ ስራ ሲሰሩ፥ እስካሁን ከእስላም ጋራ እየተጋደለ፥ በክርስትና ፀንቶ በኣለም ሁሉ የታወቀ፥ እራሱን ችሎ የኖረው የኢትዮጵያን ህዝብ፥ የክርስቲያን መንግስት፥ ስሙን ከምድር ኣጥፍተው፥ ሃይማኖቱን ኣስለውጠው፥ የእስላም ዜጋ ሊያደርጉ፤ የመንግስታችንና ያገራችንን ክብርና ስም መጠሪያ በሰንደቅ ዓላማችን፥ ላ ኢላ ሓ ኢላላ መሓመድ ረሱል ኣላህ ብለው ኣስፅፈው፥ ወስደው ለቱርክ መንግስት ቆንሲል ኣስረከቡት። ሰንደቅ ዓላማ ማለት ትርጓሜው፥ በመንግስት ፋንታ ሆኖ ለዓለም ሁሉ የሚታይና የሚታወቅ ምልክት ማለት ነው። ለዚህ ምስክር፥ መንግስት ሲባል ሰንደቅ ዓላማ የሌለው መንግስት የለም። የቱርክ መንግስትም ቆንሲል፥ ይህንን ሰንደቅ ዓላማ ተቀብሎ፥ ብዙ ደስታ ኣድርጎ፥ ሻምፓኝ ከፍቶ እያጠጣ፥ የኢትዮጵያ መንግስት የእስላም ሃይማኖት ከዓለም ሁሉ ሃይማኖት የተመረጠ መሆኑን ተረድቶት ዛሬ ኣመነ። ለዚህም ምስክር ሰንደቅ ዓላማውን ለእስላሞች ጠቅላይ ለቱርክ መንግስት ኣስረከበ። እንግዲህ ከዛሬ ዠምሮ የቱርክንና የኢትዮጵያን ወዳጅ መሆን የሚጠራጠር ሰው ቢገኝ ወንጀል ይሆንበታል እያለ በጉባኤ መረቀ። የውጭ መንግስት እንደራሴዎች ይህንን ሰምተው፥ ሰንደቅ ዓላማችሁን ኣስመልሱ እያሉ ቢመክሩ የሚሰማቸው ጠፍቶ፥ ሰንደቅ ዓላማው ኣሁንም በቱርክ ቆንሲል እጅ እንዳለ ነው።

፲ኛ

በፍፁም መሰለማቸውን ለይቶ የሚያስታውቅ፥ እስከ ኣርባ ትውልዳቸው በጠርቡሽ ላይ ኣስፅፈው፥ ወገናችሁ ነኝና እስላምነቴን እወቁ ብለው ለሃረርና እስላም ሱማሌ ሽልማት ሰጡ። ድብቅ የሌለው፥ ህዝብ ያየው ነገር ነው። ይህስ ክርስቲያኑን መካድ ኣይደለምን?

፲፩ኛ

ሃረርጌ የእስላሙን ቃዲ ጠላና ጠጅ ትጠጣለህ ኣለ። እስላምን የእስላም መፅሃፍ የማያዘውን ትሰራለህ ብለው ከሳሽ ሳይነሳበት፥ ባደባባይ ፍረዱ ብለው፥ ክርስቲያኑም እስላሙንም ኣስፈርደው ኣሰሩት። እስላሙስ ይፈረድ፥ ክርስቲያኑ በማያውቀው ሕግ ቀላቅለው በፍርሃት ማስፈረዳቸው የምን ማድረግ ይመስላል።

፲፪ኛ

ኣሁን ጅጅጋ ከወረዱ፥ የሶማሌን ውጋዝና ባላገር ሰብስበው፥ ሙሉ የጦር ልብስ ሸልመው፥ የኢትዮጵያን መንግስት ባለግርማ ሰንደቅ ዓላማችንን እዚህ ኣዲስ ኣበባ ለቱርክ መንግስት ቆንሲል የተሰጠው ኣንሶ፥ ኣስራ ሁለት ሰንደቅ ዓላማ ላ ኢላ ሓ ኢላላ መሓመድ ረሱል ኣላህ የሚል ተፅፎበት፥ ምሳሌ የሚሆን ክር ከሰንደቅ ዓላማው ተንጠልጥሎ፥ ይህንኑ ክር የሚበጥስ ፋስ የያዘ፥ ጠርቡሽ ያደረገ ሰው ስእል ተስሎበት፥ ለሱማሌዎች ሰጥቶዋቸው፥ ባደባባይ ይዘዉት መጥተው ፈከሩበት። ይህስ በክርስቲያኑ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ መነሳት ኣይደለምን?

፲፫ኛ

የኢትዮጵያን መኳንንትና ህዝብ፥ ወደ ጥፋት መሄዱን እያየና እያወቀ፥ ዝም ብሎ ትእግስት ቢያበዛ፥ ፈረንጆች የልጅ እያሱን ስራ ሁሉ ተመልክተው፥ ይህ ነገር ጃሂድ የማጠሰትና የኢትዮጵያን ክርስቲያን ኣጥፍቶ በመጨረሻ በኛ ላይ የሚከፋ ነገር ለማምጣት ነውና፥ ይህን ነገር ለመንግስት እናመልክትና፥ ለራሱ

ብልሃት ቢያበጅ ያብጅ፥ በተቀረ እኛ የምንሰራው ስራ እናውቃለን ብለው ባንድነት ሆነው በግልፅ ኣስታወቁ። ይህንን ነገር ኣስቀድመው ለመንግስት ማመልከታቸው ብናውቅበት፥ ለኛ እጅግ መልካም ነገር ነው። ክፋት ኣስበው ቢሆን ግን፥ ዝም ብለው ቆይተው፥ ልጅ እያሱም ኣሳባቸው ከፈፀሙ በኋላ፥ ባገራችን በክፉ ለመነሳት ይመቻቸው ነበር። ጃንሆይ የመሰረቱት ውል ጠብቀን ተጠንቅቀን ከኖርን ግን ኢትዮጵያን የሚነካት ሰው የለም። ባንድ በልጅ እያሱ ውል ማፍረስ ምክንያት፥ የኢትዮጵያን ህዝብ ሳይጠሉ፥ እንዴት ለምለም ኣገራችን እናስወስዳለን? ሃይማኖትስ ሲፈርስ ምን እናስተውላለን? ኣሁን ደግሞ ጃሂድ እያሉ፥ የጃንሆይን ኣሽከሮችና የክርስቲያን ደም ያፈሰሱትን እስላሞች፥ ሼኽ ጠላሃን፥ ያሰን እንጃምን ልጅ፥ ያባ ጅፋርን ልጅ፥ ደግሞ ሌሎች ብዙዎች እንደዚሁ ያሉትን ይዘው እየዋሉ፥ እዋናው የእስላም ኣገር ጅጅጋ ተቀምጠው፥ ውጋዴን ውስጥ ሽፍታ ሆኖ እያስቸገረ ከሚኖረው፥ ጅጅጋም ድረስ መጥቶ ክርስቲያን ሲፈጅ ከነበረው፥ ከከቢራው ጋራ እየተላላኩ ብዙ ጠብመንጃ፣ ጥይት፣ መትረየስ ሰደዱለት። ደግሞ የእንግሊዝንና የኢጣልያንን ዜጎች በየወሩ እየሰበሰቡ ጃሂድ እንበል እያሉ መክረዋል።

ዛሬ ጅጅጋ ወርደው መምከራቸው፥ የእስላም መካከለኛ ኣገር ነውና፥ ጃሂድ በሚሉበት ጊዜ ሃይላቸው እንዲበረታላቸው ነው። እሳቸው ግን እስላም ያረደው እየበሉ፥ ኣገር ማስፋትና ሰው ለማባበል ነው እያሉ የሚያታልሉት፥ ይህ ሶማሌና እስላም፥ ከዚህ በፊት በጃንሆይ የገበረ፥ የለቀቀ ዜጋቸው ነው። ልጅ እያሱ ግን ከእስላሙ ጋራ ኣብረው መብላታቸው፥ የራሳቸውን የእስላምነት ለማፅናት ነው እንጂ፥ ለማባበሉስ ፊት ከቀናው ኣገር በተቀረ ስንዝር መሬት የጨመሩት ነገር የለም። ኣሁንም ጃንሆይ ያሽከሮቻቸውን ደም ኣፍስሰው ያቀኑት ኣገር፥ የእስላም ሰንደቅ ዓላማ ሲለቀቅበት፥ ክርስቲያንም የሰሩት ዓብያተ ክርስቲያናት የእስላም መስገጃ ሊሆን ነውና፥ ሃይማኖት መፍረሱን፥ መንግስት መጥፋቱን ኣስበን፥ እንቻልህ እንታገስህም ብንለው የማይቻለን ሆነ። ስለዚህም ከሮፓ በፊት በወንጀል ተሰብኮ፥ ኽክርስትና ፀንቶ እስካሁን የኖረው መንግስት ሊወድቅ በደረሰበት ሰዓት ወደ እስላምነት ሲመለስና፥ የክርስቲያን ደም እንደ ጎርፍ የፈሰሰበት ኣገር ኢትዮጵያ የእስላም ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀልበት ከማየት፥ ኣስቀድሞ የሃይማኖት ኣባት ይርዳን ብለን፥ ስለ ሃይማኖትና ስለመንግስት ደማችንን ለማፍሰስ ቆርጠናል። እንግዴህ መንግስት ያለ ሃይማኖት፥ ሃይማኖት ያለ መንግስት እንዳይጠና የታወቀ ነውና፥ ለዚሁም መንግስትና ሃይማኖት፥ ጃንሆይ ኣልጋ ላይ ከዋሉ ዠምረው እስካሁን የደከሙበት ኣባታችን ነዎ። ሃይማኖት ይጥና፥ መንግስት ይርጋ ያሉ እንደሆነ፥ የማርቆስ ሃይማኖት ኣምላክ ለዳዊት እርዳታ ያወረደ መንፈስ ቅዱስ ኣይለያችሁ ብለው፥ ኣባታችን በመስቀልዎ እፊታችን ይዘው ሃይማኖታችንን ያጥኑልን።

እስላም ጃሂድ ካለ በኋላ፥ ነገሩን ለማብረድ የሰደድ እሳት ለማጥፋት እንዳያስቸግር እንደዚህ ያስቸግረናልና፥ በተሎ ካልነቃንበትና በተሎ ካላጠፋነው ስር ከሰደደ በኋላ ይልቁን ብዙ የክርስቲያን ደም ይፈስብናል። ይኸም የተነሳንበት ሁሉ በሹመት በሽረት በማግኘት ኣይደለም። ለሃይማኖታችንና ለመንግስታችን ስንል ነው። ለዚህ የኢትዮጵያ ኣምላክ ይመስክርብን።

ምንጭ፤ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ። መፅሓፍ ኣንድ። በጥላሁን ብርሃነ ስላሴ፤ 1996 ዓም፣ ኣዲስ ኣበባ። ገፅ 96-103። (Quoted from Annales D’Ethiopie by Dr. Berhanu Abebe.)